# አ ስ ታ ው ሰ ዋ ለ ሁ

ጠዋት እነቃና
ካልጋዬ እወርድና
ነፍሴን እከፍታለሁ አይኔን እዘጋና

የመላሴንም በር . . . የአንደበቴን በራፍ . . .
እቀረቅርና . . . የቃላቴን ደጃፍ . . .

እጆቼን ዘርግቼ. . . ከድኜ አይኖቼን . . .
አጥፍቼ መብራቴን . . .

በውስጤ እጮሃለሁ . . .
በነፍሴ አለቅሳለሁ . . .
እንስቀሰቃለሁ . . .

ሀፍረቴን አያለሁ . . .
ነውሬን በእጆቼ . . .ወዳንተ አነሳለሁ . . .

ቃል አልናገርም . .
ንግግር የለኝም . . .

አጆቼን ባፌ ላይ አጥብቄ እይዛለሁ
በተዘጋ አይኔ እራሴን አያለሁ . . .

በረከሰው አፌ ደሜን እቀምሳለሁ
ነውሬን እበላለሁ
እንባዬን በጽዋ እጎነጨዋለሁ . . .

በጇ የጠፋውን
በመላሴ ንድፈት የተገደለውን . . .

ያበሳዬን ዝርዝር ይዤ አቀርባለሁ
የመርገም ጨርቄንም ገልጬ አሳየሁ
በፊትህ እወድቃለሁ . . .

የቀድሞ ህይወቴን
ከሃጢያት በስተቀር . . .
ከነውር በስተቀር ቅሬት የሌለውን

የርግማኑን ዘመን . . .
አንበጣ የበላውን
ፈጽሜ አልረሳውም የሸሸቱንም ቀን

በልቤ መዝገብ ላይ እጣጥፈዋለሁ
በእንባዬ እያጠጣሁ አሳድገዋለሁ
መቼ እረሳዋለሁ . . .

እንደ ሜዳ ውሻ በውጭ ተረስቼ
በሃጢያት ስገባ በሃጢያት ወጥቼ . . .

ልክ እንደ አሞራ
ባየር ላይ እያለ አይኖቹ ታውረው
ደሙ ውስጡ ደርቆ
ክንፎቹ ተራግፈረው . .

በድንብዝብዝ ኑሮ
በጨለማ በርሮ . . .

አስታዋሽ ሳይኖረው
ወድቆ እንደሚቀረው . . .

ባይተዋር ሳለሁኝ
ወዶ የተቀበለኝ
በገበታው ስፍራ ወንበር ያሰቀመጠኝ

ከጌቶቹ መሶብ ቆርሶ ያጎረሰኝ
ከመጎናጸፊያው ቀድዶ ያለበሰኝ
ደሜን ያቆመልኝ . . .

በሳት ሰረገላ በሰልፍ ያልመጣብኝ
ሃጢያቴን ዘርዝሮ ያልተፈራረደኝ
በሞት ያልቀሰፈኝ . . .
አይቶ ያዘነልኝ . . .

የጥንት አምባ ለኔ መሸሻ የሆነው
መርገሜን ጠቅልሎ ወደ ጥልቅ የጣለው
በመስቀል ነበልባል እሳት ያቃጠለው

የዘላለም እርስት ወራሽ ያደረገኝ
ምርኮን ያካፈለኝ . . .
በከፍታ ስፍራ በቀኙ ያስቀመጠኝ

በፈሰሰው ደሙ በተበሳው ጎኑ
በብዙ መቃተት . . .
ነፍሱን ለኔ ከፍሎ
ሞቶ የመስቀል ሞት . . .

ልጁ ያደረገኝን አስታውሰዋለሁ
ከደሙ እጠቅሳለሁ
በመቃኔ ላይም ስሙን እጽፋለሁ . . .

እንደ ንጋት ኮከብ ማለዳ እወጣለሁ
ከአድማስ እስከአድማስ እወረወራለሁ
ባራቱ ማእዘናት እበታተናለሁ . . .

እናገረዋለሁ
ለትውልዴ ሁሉ ገድሉን አወራለሁ
ከበሮም በገናም እኔው እሆናለሁ
እምቢልታ እነፋለሁ . . .

ከመልከጻዴቅም የላቀ ክህነቱን
ከሰማያት ወርዶ ስለኔ መሞቱን . . .
በሶስተኛ ቀንም በድል መነሳቱን . . .

የንስሃን ዜና የስሙንም ማዳን
የሞትን መሸነፍ የሃጢያት ይቅርታን . . .

የተቀጠረውን የምህረቱን ዘመን
የጽድቅም ጸሃይ ለሁሉ መውጣቱን . . .

አዳኙ ወዳጁ በበራፍ መሆኑን
በደሙ ስርየት እርቅ መታወጁን
ቀንበር መሰበሩን . . .
የሞት ፍርድ መሻሩን . . .

ባፌ እናገራለሁ
በልቤ መዝገብ ላይ እጣጥፈዋለሁ
በእንባዬ እያጠጣሁ አሳድገዋለሁ
መቼ እረሳዋለሁ . . .

አስታውሰዋለሁ
ከደሙ እጠቅሳለሁ
በመቃኔ ላይም ስሙን እጽፋለሁ . . .

ለኔ የተደረገው
በኔ ነፍስ የሆነው
ያማኑኤል ስራ ዘመን የማይሽረው
ከታምራት ሁሉ ከድንቅም በላይ ነው

ከጠዋት እስከማታ ባወጣው ባወርደው
እልፍ ልሳን ኖሮኝ ሁሌ ብናገረው
ባወራው ባወራው . . .

አያልቅም ይህንን ነፍሴ ታውቀዋለች
እረፍት አትሰጠኝም ተነሳ ትላለች
በልቤ መድረክ ላይ ሁሌ ትጮሀለች
የመዳኔን ተስፋ ታስታውሰኛለች

ዘውዱ ሳህሉ 2002

***Back to Meskot***

---

***The views reflected in the above poem/article are solely of the author and are not necessarily shared by*** *Meskot****. You may contact Zewdu Sahlu  for comments at*** *zewdu_michael@yahoo.com*